የፍቅር ልጆች ማህበር /Daughters of Charity/ ትግራይ ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን - የልማትና ማህበራዊ ኮሚሽን ዓዲግራት ቅርንጫፍ /Ethiopian Catholic Church Social and Development Commission of Adigrat Branch/ ለተማሪዎች የምገባ ፕሮግራምና የምግብ እጥረት ላለባቸው ሴቶችና ህፃናት አገልግሎት የሚውል ፋፋ /Famix MS 5%/ በግልፅ ጨረታ አወዳድረን ለመግዛት ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ሓሙስ ነሓሰ 15, 2017 (ከ 1 ዓመት)
- መዝግያ ቀን: ነሓሰ 20, 2017 8:30 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:50,000.00
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ነሓሰ 21, 2017 9:00 ጥዋት
- ምድብ: ኣቅርቦት ምግቢ /

የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

የፍቅር ልጆች ማህበር /Daughters of Charity/ ትግራይ ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን - የልማትና ማህበራዊ ኮሚሽን ዓዲግራት ቅርንጫፍ /Ethiopian Catholic Church Social and Development Commission of Adigrat Branch/ ስር ሆኖ ለሚሰራቸው የተለያዩ የልማት፤ ማህበራዊና ሌሎች የሰብአዊ አገልግሎቶች አርዳታ እየሰጠ ይገኛል፤ ከሜርስ ሚልስ ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅት /MMI/ ጋር በመተባበር በ20 ወረዳዎች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ያሉ በርካታ ተማሪዎች የሀገር ምርት በሆነ የምግብ ዓይነት ቀን አንድ ጊዜ የመመገብ ሰራ በመስራት ላይ ይገኛል።

ድርጅታችን ለተማሪዎች የምገባ ፕሮግራምና የምግብ እጥረት ላለባቸው ሴቶችና ህፃናት አገልግሎት የሚውል ፋፋ /Famix MS 5%/ በግልፅ ጨረታ አወዳድረን ለመግዛት ስለፈለግን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የምታሟሉ ፋብሪካዎች እንድትወዳደሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

1. ፋፋ /Famix MS 5%/ ለማምረት የ2017 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላችሁ።

2. ቫት ተመዝጋቢ የሆነ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያለውና ህጋዊ ተከታታይ ደረሰኝ ማቅረብ የሚችል።

3. ተጫራቾች ለምርቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፍኬትና በቀን ፋፋ የማምረት አቅም ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው

4. ተጫራቾቸ ጨረታው ከተከፈተበት በኋላ ማስተካከያ ማድረግ፤ ራስን ከጨረታ ማግለልም ሆነ መቀየር አይቻልም።

5. ተጫራቾች ውል ከማሰራችን በፊት አጠቃላይ የፋብሪካው ደረጃና የማምረት አቅም ምዘና አንደምናካሂድ ማወቅ ይኖርባቸዋል።

6. ተጫራቾች ጨረታ ማስከበርያ በ CPO 50,000.00 ብር በድርጅታችን ስም አሰርተው ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማቅረብ አለባቸው።

7. ጨረታውን ያሸነፈ ዋጋ ፀንቶ የሚቆየው ውል ካሰረበት ቀን ጀምሮ ለስድስት ወር መሆኑ ማወቅ አለባቸው።

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

8. ተጫራቾች ዋጋ የሚያቀርቡትና ውል የሚያስሩት ለአንድ ኩንታል ቢሆንም በሚታዘዘው መጠን (Order) መሰረት የተጠየቀውን ሁሉ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።

9. ጨረታ ያሸነፈው ምርቱ አዲስና ቢያንስ 6 ወር የአገልግሎት ጊዜ ያለው በውስጥ ደረጃውን የጠበቀ ፕላስቲክ ከላይ ደረጃውን የጠበቀ በ50 ኪ/ግ ማሸግያ በመጠቀም የድርጅታችን 3 ሎጎዎችንና በቻ ቁጥር በማተም ማቅረብ የሚችል።

10. ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ መቀለ ዓዲ ሓቂ ከፍለ ከተማ ካቶሊክ የዓይን ህክምና በስተጀርባ የሚገኘው የፍቅር ልጆች ማህበር ትግራይ ክልል ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት ወይም አዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 374 ካቴድራል ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ከ 12/12/2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 20/12/2017 ዓ.ም ድረስ መውሰድ ይችላሉ።

11. ጨረታው በመቀለ በዋና ፅህፈት ቤት በ 20/12/2017 ዓ.ም ከቀኑ 8:30 ተዘግቶ በተመሳሳይ ቀን 9:00 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፤ ሆኖም ተጫራቾች ባይኖሩም ጨረታው ይከፈታል።

12. የፍቅር ልጆች ማህበር ትግራይ ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ማሳሰቢያ የዋጋ ማቅረቢያ ቅጅ ከአዲስ አበባ ጽ/ቤት መውሰድ ይቻላል።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የልማትና ማህበራዊ ኮሚሽን ዓዲግራት ቅርንጫፍ

የፍቅር ልጆች ማህበር / Daughters of Charity/ ትግራይ ማስተባበርያ ጽህፈት ቤት

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle